# ከፋኝ!

አይሉት ትምርት ቤት
ድግሪ የማገኝበት
አይሉት ግብርና
የለው ሞፈር ቀንበር
ለቅቄ ከወጣሁ የኢትዮጵያን ሐገር
ቀንም ሆነ ለሊት፤
ለሥራ እሮጣለሁ በየ አረቡ ቤት።

## ከፋኝ!

አረ ምን ይብጀኝ?
እሪ የሰው ያለህ
እጅግ አርጎ ክፋኝ ከቶ ምን ይብጀኝ?
ሥራው ብቻ ሳይሆን
ለውርጋጡ ሁሉ መጫወቻ አረጉኝ

## ከፋኝ!

አረ ምን ይብጀኝ?
ብሶቴን በዝርዝር
ለሽሁ ብነግር
ተንጋለው በሣቅ እንዲህ አፌዙብኝ፤
ኮረዳ ከድኛ ምነው ዛሪስ ድግሞ
እንደ ነፍስ አባትሽ ጉድሽን አዋየሽኝ!

## ከፋኝ!

አረ ምን ይብጀኝ?
ጠፍቸ እንዳልሄድ መለዮየን ይዘው፤
ይሣለቁብኛል እንደዚህ እይሉ
ዝም በይ ከድኛ
ያለሽበት ይዘት ለጥቁር መች አነሰው።
ይግረምሽ አሉና በጥፊ ቀላቅለው፤
የሥራየን ዝርዝር በወረቀት ጽፈው
ቁመው አስገደዱኝ ጩሄ እንዳነበው
ዝርዝሩም እንዲህ ነው...
ለሁለት ቤተሰብ ይህን ታደርጊያለሽ፤
ቤቱን አጸዳድተሽ
ምግቡን በያይነቱ ቀምመሽ አብስለሽ

ትንሾቹን ልጆች አጥበሽ አለባብሽ
በጊዜ መግበሽ
እንድትዘጋጅ ለወንዶቹ ልጆች
አንድ እንኮዋን እንዳትረሽ
ወላሂን ነገርነሽ!

**ከፋኝ!**

እሪ የሰው ያለህ
ከቶ ምን ይብጀኝ?
እንዲያው ምኑ ይሆን ለዚህ የዳረገኝ!

ከዘመድ አዝማዱ ገንዘብ ተበድሪ
የመንግስት ግዳጅን ባንድ ጊዜ ከፍየ
ስሜንም ለውጨ እንዲያመቸኝ ብየ
ክርስትናን ትቸ
በርሃብ ከመገረፍ ስደትን በመረጥሁ
ይኸ ሁሉ ስቃይ በኔ ላይ መድረሱ
አረ ማንን በደልሁ!

**ከፋኝ!**

እሪ የሰው ያለህ
ከቶ ምን ይብጀኝ?

© ለምለም ጸጋው
በድህነት ምክኒያት ተሠደው በመካከል ምሥራቅ ለሚሰቃዩ
ኢትዮጵያውያን ሲቶች መታሰቢያ ይተጻፈ
ሐምሌ 17, 1999 (July 27, 2007)

# አልሞላም ከዘናሽ!

ድህነት ሰልችቶት አዲሱ መዋቅር፤
ካድሪውን አዘዘ
ለማኝ እንዲለቅሙ በየከተማው በር።

ይገርማል ይደንቃል የኢትዮጵያ ይዘት፤
አዲሱ መዋቅር ጠላና ድህነት
ገንዘብ ለመለመን በሰለጠነ መልክ

ኢሮፕ ተሻገረ ደንቅሮ ከራባት።

አገሬ ኢትዮጵያ ምን መዋቅር አቆዋቆዋምሽ፤
ሁሉ እንኮዋን ተሽጦ አልሞላም ከዘናሽ።

አዲሱ መዋቅር እኔ አውቃለሁ ብሎ
አዘዘ ገበሪን፤
አበባ እንዲተክል
ትቶ ጤፍ መዝራቱን።

ይገርማል ይደንቃል የኢትዮጵያ ይዘት፤
አዲሱ መዋቅር ሊያጠፋ ድህነት
በሰለጠነ መልክ ደንቅሮ ከራባት
ልመናን ቀጠለ በአሜሪካ መሬት

ይገርማል ይደንቃል በጽሞና ላየው የኢትዮጵያን ነገር
ድህነት ሰልችቶት አዲሱ መዋቅር፤
ካድሪውን አዘዘ
ለማኝ እንዲለቅሙ በየከተማው በር።

አገሬ ኢትዮጵያ ምን መዋቅር አቆዋቆዋምሽ፤
ሁሉም ተሻሽጦ አልሞላም ከዘናሽ።

© ለምለም ጸጋው
ሐምሌ 17, 1999 (July 27, 2007)